# ማን ከማን ይጣመር ?

ላፑና ከሀገር ፍቅር

የምርጫ ቦርድ የዘንድሮውን የተሳካ ምርጫ በድል ለመደምደም የቤት ስራውን እያጠናቀቀ ነው:: በግንቦት ሰባቱ ምርጫ ብዙ ወንበሮች ቢያጣም ኢህአዴግ መንግስት መመስረት የሚያስችለውን ድምጽ አግኝቷል::

የዘንድሮውን ምርጫ ስኬታማነት ለማኮሰስ እንቅልፍ አጥተው በቀቢፀ ተስፋ እየተንቀሳቀሰ ያሉው ቅንጅትና በእሱ ውስጥ ለመወሸቅ የሚዳዳው ህብረት ደግሞ በግርግር እና ትርምስ የስልጣን እርካብ ለመቆናጠጥ ያላቸው ፍላጐት መምከኑ ባይቀርም የመጨረሻቸውን ጥረት እያደረጉ ናቸው::

ምርጫው አሁን ባለበት ሁኔታ ወደ መጠናቀቅ መቃረቡ እና እነሱ በሚፈልጉት መልኩ ሁከት አለመነሳቱ ያበገናቸው ሁለቱ ታቃዋሚ ቡድኖች የምርጫውን ውጤት እንደማይቀበሉ በጋራ ገልፀዋል:: ተቃዋሚዎች የምርጫውን ውጤት በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት የማይገሰስ ስልጣን የምርጫ ቦርድ መሆኑን ሳያውቁት ቀርተው ነው ብዬ ራሴን ለትዝብት አልዳርግም :: የዕውቀት የመጨረሻ አናት ላይ ደርሶናል ብሎው ከሚመጻደቁት ልሂቀንና ጠቢባን ሰዎች አይጠበቅም ብዬ ነው:: እርግጥ ነው ተቃዋሚዎች አንድ አማራጭ አላቸው:: ይህ አማራጭ ሁከት ብጥብጥ ወይንም እሳት አቀጣጥሎ ዳር ሆኖ መሞቅ ሳይሆን ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ይሆናል::

ተቃዋሚዎች ህገመንግስቱን ተፃረው በዚህ ህገመንግስት እና በአገሪቱ ህግ የተቋቋሙ ተቋሞችን ውሳኔ ሳያከብሩ መሄድ እንደማይችሉ ሊገነዘቡ ይገባል:: የህገመንግስቱ አንቀጽ 9 የሚለው ይህንኑ ነው " ማንኛውም ዜጋ የመንግስት አካላት የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ሕገመንግስቱን የማስከበርና ለህገመንግስቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው:: " አራት ነጥብ:: እዚህ ላይ መንግስት መነቀፍ ካለበት በህጉ ቃልና መንፈስ መንቀሳቀስ ሲገባቸው ከመንገድ የወጡ የተቃዋሚ ፓርቲ እና መሪዎቻቸውን ከሚገባው በላይ ተሸክሟል::

የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ህገመንግስቱን ህገ አራዊት፣ እንዲሁም ህገ መንግስቱ የተፃፈበትን ወረቀት ያህል ዋጋ የለውም እያሉ ውሃ የማይቋጥር ንግግር ሲደረድሩ ዝም ማለቱ፣ የአገር መከላከያ ሠራዊት ህግና ስርዓት ለማስከበር የሚያደረገውን ጥረት አጠናግረው የተወሰነ ብሄር ጦር አድርገው ሲያቀርቡ በሆደሰፊነት ተውኩ ቢል አይዋጥልኝም:: ታቃዋሚ

ፓርቲዎች በቃችሁ ሊባሉ ይገባል። ህግወጥ ተግባራቸውን በህጋዊነት ሽፋን ማራመድ አይችሉም። ሁለት እግር አለኝ ተብሎ.... አይደል ብሂሉ።

የታቃዊሚ ፓርቲዎች ሁለት መገለጫዎች አላቸው። የመጀመሪያው እነዚሁ የቀድሞ የደረግ ስርዓት አቀንቃኞች አላማቸው በዚህም ሆነ በዚያ ብለው ስልጣን መያዝ ነው።ይህን ሂደት ከመደገፍ ውጭ መቃወም አይፈቅዱም ። እንኳን መቃወም በሃሳብ መለየትን አይታገሱም። የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር ምርጫውን ዲሞክራሲያዊ ባሉ ማግስት ከባድ ወርጅብኝ ነው የጠበቃቸው። የአውሮፓ ህብረት ልዑክ ኃላፊ ቲሞቲ ክላርክም የማጣራት ሂደቱ ከባድ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም በተሳካ ሀኔታ እየሄደ ነው ሲሉ ተመሳሳይ ነገር የጠበቃቸው። ሰሞኑን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለኢህአዴግ ካቀረቡት ሃሳብ ጋር በተያያዘ ጉራ ለይተው የግል ጋዜጦች አቶ ልደቱ አያሌውን ኢትዮሚድያ እና ኢትዮጵያ ሪቪው የተሰኙ ድረ-ገጾች ደግሞ ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ውጉዝ ከምአረዮስ አያሏቸው ነው።

በግሌ በተቃዋሚዎች ጉራ ልዩነት ውበት መሆኑ የሚታወቅበትን ቀን እናፍቃለሁ። በምርጫው ዋዜማ ለኢህአዴግ ባላቸው የባላንጣነት ስሜት የተቀናጁ የመሰሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምርጫው ወደ መጨረሻ ምዕራፍ ሲደርስ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ኢህአዴግ አምስት ዓመት እንዲመራ ይሁንታቸውን ሲገልፁ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ ዓለምአቀፍ ማህበረሰብ ምርጫውን ማወደሱ ይፋ ሲሆን የተጣበቁበት ሙጫ ለቆ መናቆር ጀምረዋል። ይባስ ብለው የቅንጅት መሪ አቶ ሻውል ለኢህአፓ የትንሳኤ ሬዲዮ በሰጡት መግለጫ የአፍሪካ ህብረትን የአምባገነኖች ክበብ ሲሉ ዘልፈዋል።

አሁን አሁን ቅንጅትና ህብረቱ ስልጣን በአቋራጭ ለመያዝ ከመፈለግ በተጨማሪ ስለምርጫው አመት ሙሉ ሲነገር እንዲኖር የሚፈልጉ ይመስላሉ። አንድ ምዕራፍ በተጠናቀቀ ቁጥር ምክንያት እየፈለጉ ሌላ ይጨምሯሉ።

የምርጫው ዋዜማ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ቅድመ ሁኔታ አቀረቡ ኢህአዴግ ተሰማማ። ምርጫው ተጠናቀቀ ተጭበርብሯል ይመርመር አሉ። ምርመራ ሲጠናቀቅ እነሱ ለማደናቀፍ ቢሞክሩም ተገፍተው ገቡ። መጨረሻ ካሳሸቹ ራሳቸው ተከሳሽ ሆነው የሽንፈትን መሪር ጽዋ ተጋቱ ። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ሌላ ቋጠሮ በመጀመር የብሄራዊ አንድነት መንግስት ይቋቋም የሚል ፋሽን የጀመሩት። ይህ የተቃዋሚዎች ጥያቄ ከህግም ከሞራልም አንፃር የተሳሳተ ነው።

ተቃዋሚዎቹ የአንድነት መንግስት ይመስረት ሲሉ ያቀረቡት ሃሳብ በተግባር ለህገመንግስቱ ክብር የሌላቸው መሆኑን ያሳየው። የአገሪቱ ህገ መንግስት አንቀጽ 56 በፓርላማው አብላጫ ወንበር ያለው ፓርቲ መንግስት ይመሰረታል ይላልና። ኢህአዴግ የድጋሚ

እና ማሚያ እንዲሁም የሶማሌ ክልል ምርጫ የሚኖረው መቀመጫ ሳይሰላ እንኳ የአብላጫ ድምጽ አግኝቷል፡፡ በምርጫው ያጡትን የህዝብ ድምጽ በምልጃና ደጅ መጥናት ለማግኘት መሞከር ታዲያ ምን አመጣው?

ተቃዋሚዎች አሁን ያቀረቡት ህዝባዊ "መንግስት ይመስረት" የሚለው ሃሳብ የዛሬ 30 ዓመት ታሪክን ወደ ኋላ አስታውሰኝ፡፡ ያኔ ኢህአፓ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የዛሬን አያድርገውና ደርግ ስልጣን በአቋራጭ ይዞ ምንም አይነት አማራጭ የከለከለበት ሁኔታ ስለነበረ ነው፡፡ ዛሬ ደርጐች እንኳን ይህን አማራጭ ሳይነፈጉ ፓርቲ አቋቁመው ተወዳድረው ተሸንፈዋል፡፡ ያኔ በአውደ ግንባር ዛሬ ደግሞ በአውደ ምርጫ፡፡ ስለዚህ የተቃዋሚዎች ጥያቄ አራምባ እና ቆቦ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ከሞራል አንፃር ተቃዋሚዎች "በክህደት፣ በአገር ማስገንጠል ብሎም በቅኝ ገዢነት ፈርጀው እንደመስሰዋለን" ከሚሉት ኢህአዴግ ጋር እንዴት ሊሰሩ ፈለጉ? ጉድ ነው! ከምርጫው በፊት የነበረው ኢህአዴግ ሰሞኑን ተለወጠ ወይስ እነሱ ተለወጡ፡፡

ቀደም ሲል ለመገለጽ እንደተሞከረው ስልጣን ወይም ሞት ያሉ የሚመስሉት ህብረት እና ቅንጅት ባቀረቡት ረቂቅ ሃሳብ የካቢኔ ስልጣን ሁለቱ ፓርቲዎች እና ኢህአዴግ ብቻ ባገኙት ወንበር ልክ እንዲሆን ወስነዋል፡፡ እንዲህ ይነበባል፡-

> The new government shall be structured in such a way that cabinet posts and portfolios are shared equitably among the three major parties in accordance to the proporition of the votes they received at the May election.

ለነገሩ ተቃዋሚዎች በተለይም ቅንጅት የዛሬውን አያድርገውና ጠቅላይ ሚንስትሩን ብሎም የሚንስትሮቹን ማንነት ከግንቦት 7 በፊት መወሰኑን ነግሮን የለ፡፡ ህብረቱም ቢሆን በኢትዮጵያ ረቪው ድረ-ገጽ ካቢኔውን ከሰየመ ቆየ፡፡ ነገርን ነገር የነሳዋል አይዳደል የሚባለው አንድ ባልደረባዬ የተቃዋሚ መሪ የሆኑት የአዲስ አበባ የዩኒቨርስቲው ፕሮፌሰር" ተስፋኛው ጠቅላይ ሚኒስቴር " /Aspiring Prime Minister/ መባል ከጀመሩ ቆይተዋል አሉ፡፡

ቅንጅትና ህብረት ባቀረቡት ሃሳብ የስልጣን ጥማቸው እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ፍንትው ብሎ ታይቷል፡፡ "ኢህአዴግ እንኳን አሸንፎ ብሸነፍም አልጣመርም" አለ እንጂ የስልጣን ክፍፍሉ በሶስቱ ፓርቲዎች መሀከል ብቻ ይሁን ነው ያሉት፡፡ ኦፌዴን ? ጋህዴን? አብዴፓ? ሰአን ወዘተ... ያገኙት ድምጽ ዋጋ የለውም? ከነሱ ጀርባ ያሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ መራጮች ድምጽ የት ይድረስ? ከህብረትና ቅንጅት መልስ ይጠበቃል፡፡ ኢህአዴግ ከማን ጋር ተጣምሮ

መስራት እንዳለበት የእስካሁኑን ተሞክሮ ዞር ብሎ ማየት በቂ ስለሆነ ዕርም ማውጣት ይሻላል። ማን ከማን መጣመር እንዳለበት ደግሞ ሂደቱ የመለሰው ጥያቄ ነው። ኢህአዴግ በታሪኩ ከፀረ-ሠላም እና ፀረ-ዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር ግንባር እንዲፈጥር ባህሪው አይፈቅድለትም።

የታቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቡት ከአንድነት መንግስት ጋር የተምታታ ሌላው ጥያቄ የሽግግር መንግስት ነው። ጉበዝ ዝንተዓለም ስንሻገር ልንኖር ነው ? የኢትዮጵያ ህዝቦች በ1983 ተሻግረዋል። ይልቅ ያልተሻገሩት ተቃዋሚዎች ይሆኑ?

ተቃዋሚዎች ተጨንቀን ተጠበን አቀረብነው የሚሉት ሃሳብ አሮጌ ወይን በአዲስ ጠርሙስ አይነት ነው። የሽግግር መንግስት ጥያቄ የሽግግር ዘመኑ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ደጋግመው አንስተውታል ። ዘንድሮ ምን አዲስ ነገር ተገኘ?

ሁለቱ ፓርቲዎች ያነሱት የብሄራዊ ርዕቅ ጥያቄም ረብ የለውም። ስለምን በግንቦት ምርጫ ህዝቡ ድምጽ የሰጠው ለአንድነት መንግስት ምስረታ አልያም ለብሄራዊ ዕርቅ አይደለም። በኢትዮጵያ ማንም ዜጋ የአገሪቱን ህግና ህገመንግስት እስካከበረ ድረስ ምንም እንደማይደርስበት በደርግ ውድቀት ተረጋግጧል። ለዚህ ቢያንስ እነ የተከበሩ ኃይሉዎች እማኝ ናቸው።

ይህ የይቅርታ ጥያቄ እንደ ሌላ የታቃዋሚዎች የምርጫ ስትራቴጂ ሁሉ ከነገደ ጉበዜ የምርጫ መዝገብ ቃላት የተቀዳ ግን የማይሆን ነው። ዛሬ ቀልቤሳ ነገዎ ነው፣ ነገ ደግሞ ማን ያውቃል በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ስም ኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዛቸውን በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ለመጫን ዘመቻ የጀመሩት ሌሎች ፋሽስቶች ይከተሉ ይሆናል።